❖ ***የሀገራዊነትና የታሪክ ዕይታ***

***... ኢትዮጵያ ረጅም ዕድሜና ታሪክ አላት። በተለያዩ ነገሥታትና ሥርዓቶች በሚገለፀው በዚህ ሀገራዊ ጉዞ ከዛሬው የሰፋም ሆነ ያነሰ ግዛታዊ መጠን ነበራት። ለዚህ በየዘመኑ ተለዋዋጭ ግዛታዊ ቁመና እና ተያያዥ ሀገራዊ ማንነት አቀጣጣይ የሆኑ ወቅታዊ ግፊቶች ቢኖሩም ዋነኛው መንስኤ ኢኮኖሚያዊ አቅም ባለቤትነቷ መዳከም ወይም መጠናከር ጋር የተያያዘ ነው። ከዚህ የሚመነጭ አንድ የማያጨቃጭቅ ሀቅ ቢኖር ግዛታዊ መቀነስ ወይም መጨመር የኢትዮጵያ ታሪክ አካል የሆነ እውነታ መሆኑ ነው። (አንዳርጋቸው ያጤኗል)።...***

------------------------------ /// ------------------------------

*... ከድህረ ጣሊያን አንስቶ እየተንከባለለ እኛ ጋር የደረሰው ''ኢትዮጵያ ሀገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ'' የሚል ''የከሃዲዎች የበላይነት'' ግንዛቤ በደርግም በድህረ ደርግም ስር እየሰደደ ሊመጣ ተቻለው...። ይህ ደግሞ በአንድ በኩል ዛሬ የምናየውን የተስፋፋ እውነትን ያኮሰሰ ምፀተኛነት እና የመመሳሰል አድርባይነት ሊያደነድን የቻለ የግንዛቤ ነዳጅ ነው። በእንድምታም ደረጃ የጥቂት ከሃዲዎች የበላይነትና ውጤታማነት ተደጋግሞ ''በመግዘፍ'' የህዝብ የተቀናጀ ጥረት አሸናፊነትን የሚያኮስስ አስተሳሰብ ማገዝ ይሆናል። ...*

------------------------------ /// ------------------------------

***... ለታሪካችንና ለሁሉም ገፅታዎቹ የሚገባውን ክብር መንፈግ የለብንም። በማይገባው፣ ባልሆነውና በማይመጥነው መልኩ እኛንም ሆነ ትውልዳችንን እንዲጫን ሳንፈቅድለት ማጣጣም ተገቢ ነው። ጥሩ የቀደምት ትውልዶቻችን ወራሽ እና ጥሩ ባለአደራ ሆነን አዎንታዊ በሆነ ዘላቂነት መስዋዕትነታቸውን ለክብር፤ ታሪካቸውን ደግሞ ለፍሬያማነት የምናበቃው ይሄን ማድረግ ሲቻለንና ሲሆን ብቻ ነውና። ... የተወሰኑ ከሰፈሩልን ታሪክ ውጪ እንድናውቅ ስለማይፈልጉ ሁሌም ከመመሳሰል ታሪክ ጋር ተቃቅፈንም ሆነ ትላንታችንን እየፈራንና አይነኬ ብለን እየሸሸን መኖር የለብንም። አለፍ ሲልም ልናመልከው አይገባንም። ...***